# እንኳን ሲሸጡኝ ሲሰማሙብኝም አውቃለሁ

ወንድሙ መኰንን ከሎንደን

ጀሮ ጭው የሚያደርግ ዜና ሰሞኑን ሰማን። ጀሮ መቼም አይሰማ የለ፣ ሰማን ጉድ! ጆሮአችንን ማመን እያቃተን ባለንበት ስንተሻሽ የባሰውኑ "ቀራጡ መሪ" እየተባለላቸውኢንጂነየር ኃይሉ ሻውል፣ የመላ ኢትዮጵያው ፓርቲ ፕሬዝደንት፣ ከሌሎቹ መሰል አገር ወዳድ የተገፉ የትግል ጓዶቻቸው ጋር ሳይሆን፣ ቅንጅት ሲገደል ሥጋውን ከተከፋፈሉት የወያኔ ቅምጥልና አስመሳይ የውሸት ተቃዋሚዎች፣ የቅንጅት የጣት ምልክት ባለቤት፣ ከነአቶ ለደቱ አያሌው፤ የቅንጅት (ከወያኔ ውጭ ከነማን እንድተቀናጁ አንድዬ ይወቀው) ስም ብቸኛ ባለቤት ከሆኑት ከነአቶ አየለ ጫሚሶ ጋር ተጎልተው አሳፋሪ ስምምነት ሲፈራረሙ፣ ዓይን አይከለከል፣ በዚችው መከረኛ የዓይናችን ብረት በቴለቪዥን መስኮት አየናቸው። "አንበሳው አገሳ" እየተባለ ይዘፈንላቸው የነበሩት ኃይሉ ሻውል፣ የጥንቸልንም ያክል ሳያንገራግሩ፣ በፍረንጆቹ ኩርኩም ተገጭተው ለመለስ ዜናዊ እጅ ሲነሱ፣ አብረውም በአንድ ጠረጴዛ በመቅመጣቸው፣ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሥቃዩን ሲያመሰግነት ዓይተን ግራ ተጋባን። "አንበሳው ልጅሽ፣ በርግጎ ገደል ገባልሽ" ይሉሻል ይኸ ነው። አንዲት ቀን እንኳን ብዕሬን "ተቃዋሚ" መሬዎች ላይ (አቶ ልደቱንም ሳይቅር) አንስቼባቸው አላውቅም። ዛሬ ግን፣ ትልቁ ዳቦ ሊጥ ስሆንብኝ ከፋኝ። ከረፋኝ። አንግሸኝ። ዝምታ ለበጊቷም አልበጃትምና፣ ይቀለኝ እንደሆን እስቲ የለቤን ቁስል ላካፍላችሁ።



የእንጀራቸው ኢንጂነየር የሆኑት ቱጃሩ ኃይሉ ሻውል የተፈራርሙት "የምርጫ ሥነ-ምግባር ድንብ" ለኢትዮጵያ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ አሸቃባጮቻቸው ይነግሩናል። እንዲያውም "ጉድ ነው ሲዳሩ ማልቀስ፣ ሲታጩ ደስደስ" ይላሉ አበው ሲተረቱ። "ማንዴላ የሠሩትን ጅግነነት ኢንጂነየር ኃይሉ ደገሙት" ብለው ትንሽ እንኳን ሳይፍሩ ቅንጅት ዓለምአቀፍ ላዕላይ ምክር ቤታቸው ከአሜሪካ የድጋፍ መግለጫ አወጡላቸው። ኤዲያ!!!!! በዕውነትም ደጎና ሰው ሲበላሽ ቅራሪ የለውም። ምኑን ከምን አመሳሰሎት አረፈው፣ ጃል!! የማይመስለውን ነገር!! ምናለ አሁን በዱልዱም ስለት ባይገዘግዙን! ማንዴላ 27 ዓመት እሥር ቤት በግፍ ታሥሮ እንዳመጸ፣ "የአፓርታይድ ሥርዓት መገርሰስ አለበት" በማለት በቆራጥነት እና በሙሉ ልብ ታግሎአቸው፣ በጅግነነት አንዲት ስዝንር እንኳን ከዓላማው ለጠላት ፈቀቅ ሳይል፣ እንደተነበየው አፓርትይድን ገረሰሶት በድል አድርጊነት ከእሥር ቤት ወጥቶ የደቡብ አፍሪካን ሕዝብ ፍላጎት ሳይሸጥ ነጻነቱን አጎናጽፎ የመጀመሪያ ፕሬዘደንት ለመሆን ቻለ እንጂ፣ አፓርታይድ እንዳለ ተቀላቅሎት ሕዝቡን አልሸጠም። እሱ እንደ ሻማ ቀልጦ ሕዝቡን ብርሀን አለበሰው እንጂ፣ [የቢዝነስ ኤምፓየሩን ለመጠብቅ፣]() ሒሊናውን አዋርዶ ለአፓርታይ የመተንፈሻ ሳምባ አልዋሰውም። ምን አለ የማንዴላን ስም አሁን ባያቆሽሹት! ታዲያ የኛ ማንዴላ ከአፓርታይድ ያልተናነሰ የወያኔ ሥርዓት እያለ የሥልጣን ጥማቸውን ለመውጣት አለበለዚያም ኃብታቸውን ለመጠበቅ (ሀብታም መንግሥተሰማያት ከሚወርስ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብትሾልክ ይቀላታል ነው ያለው ክርስቶስ?) ተባባሪ ሊሆኑ ካልሆነ በስተቀር በየትኛው ሒሳብ ነው ከማንዴላ ጋር የሚስተካከሉት?

አሁንም "ከአፈርኩ አይመልሰኝ" ደጋፊዎቻቸው፣ ኢንጂነሩ ብዙ ጥያቄ አቅርበው ስምምነቱ ላይ ወያኔ እጁን ሰጥቶ ነው የተፈራረሙት እያሉ ዓይነቸው በጨው ታጥበው ሊያደርቁን ይሞክራሉ! ምንድነው ወያኔ የተቀበለላቸው ጥያቄ?! ወይስ እሳቸው የወያኔን አምባ ገነን ሥነ-ሥርዓት እንዳለ ተቀበሉትና ያ ተግልብጦ ተነበበላቸው!? በቸኛው ቆራጥ መሪ እንዳልተባሉ፣ ብቻቸውን አብረው የታሠሩትን ጓዶቻቸውን ትተው የወያኔ ሠርግ አጃቢሁነው ተገኝተዋል። አለቀ! ደቀቀ!

ደረቅ ጽሑፍ ማንበብ ይሰለቻልና፣ እንዲያው ትንሽ ወጣ ብለን ተናፍሰን ለመመለስ ያህል፣ አንድ የተለመደ ጨዋታ እዚህ ላይ ላንሳ። ሰውየው ልኳንዳ ቤት ይሠራል አሉ። ኣጥንቱንም፣ ሥጋውንም ሲቆራርጥ አንዳንዴ በደም የተነከረውን ልብስ ሳይለውጥ እንደለበሰ ቤት ይገባል። መከረኛ ሚስት ያንን እየተቀበለች ታጥባለች። "እንዲያው ምንድነው ይኸ ሁሉ ደም" ብላ ስትጠይቅ፣ አንዴ ወንበዴዎች መንገድ ላይ አጋጥመውኝ ሊገድሉኝ

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ሲሞክሩ ጨፈጭፍኳቸው፣ ሌላ ጊዜ ጠላቶቼን መንገድ ላይ አድፍጠው ሲጠብቁኝ ቀደሜ ፈጀሁአቸው” እያለ እያጭበረበራት ኖረ። ሚስት ብዙም ሳትመራመር አክብራ ውሸቱን ተቅብላ ኑሮዋን ተያያዘቸው። አንድ ከሱ ጋር ያደገ የመንደር ተደባዳቢና አውደልዳይ ወጠምሻ፣ የባሏን ልብ በቅርብ ስለሚያውቅ፣ ይኽችኑ ሴት ሊያማግጥ ይምክራል። ሲትዮዋም ባለቤቷ በጣም ኃይለኛ እንደሆነና እንደሚገድለው አስጠንቅቃ በጤናው እንዲተዋት ታሥረዳዋለች። አውደልዳዩ ጉልቤ በጣም ስቶ ለጊዜው ይተዋታል። አንድ ቀን ባልና ሚስት ለፋሲካ አክፋይ ተያይዘው ወጣ ወዳለው መንደር፣ ወደሴቲቱ ቤተሰብ ሲሄዱ አንድ ጭር ባለ ቦታ ላይ አባ ጉልቤ በድንገት ከተፍ ይልባቸዋል። “አንድ ነገር ካለ ዛሬ ይኸ ባለጌ ጉድ ፈላበት” ብላ ወይዘሮ ሚስት ስትጠብቅ የልጠበቀችው ጉድ በሷው ፈላባት። ታዋቂው ሞጭልፌ ባሏን በስሙ ይጠራውና “መሞት ካልፈልግክ ና ከበቅሎህ ውረድና የማዝህን ሁሉ ፈጽም” ብሎ ሲጮኽበት፣ አቶ ባል ሆዬ ሳያንገራግር ደንግጠ ዱብ ይላል። ልብሱን አውልቆ እዚያው ሚስቱ እያየች እንዲጸዳዳ ሲያዘው ባል ተብዬው ምንም ሳያቅማማ እንደታዘዘው ያደርጋል። ያም አልበቃ ብሎት፣ ጉልቤ “በል ዘንብ እንዳይርፍብት፣ ‘እሽሽ እያልክ ጠብቅ” ይለዋል። እሺ ብሎት ትዕዛዙን ሲፈጽም ዱሮየው እዚያው እፊቱ ሴትዮዋን ጠምዝዞ፣ እየታገለቻው ተሸንፋ ይደፍራትና የልቡን አድርሶ በቅሎውን ቅምቶት ጉብ ብሎባት ይኸዳል። የተናደደችውና በሴትነቷ መደፈሯ ያንጨረጨራት ልጅት በንቀትና በምሬት “ከዚህስ ብትሞት ይሻለሀል። እሺ ያንን ሁሉ አደረሰብህ፣ ከሁሉ የገረመኝ ክርፋትህን ዝንቦች እንዳይበሉ “ጠብቅ” ሲልህ እሺ ብለህ መታዘዝህ ነው” ትለዋለች። ደደቡ ባል ሆዬ፤ “የጠበቅኩት መሰለሽ? አስበልቼው - አስበልቼው” አለ ይባላል። ጨዋታ ጥሩ ነው። እያዝናና ያስትምራል።

ወደ ዋናው ቁምነገር ከመመለሴ በፊት በተገላቢጦሽ የጎንደርን ጀግንነት ላውሳላችሁ (እኔ ጎንደሬ አያደለሁም)። ወያኔ ዳሽን የተባለውን ቢራ ፋብሪካ ያቋቁምና ከትግራይ በመጡ አስተዳዳሪዎች፣ መሀንዲሶች መጠጡን እያመርተ በትግራይ ዘበኞች እያስጠበቀ ምርቱን ለጎንደሬ ገቢያ ያቀርባል። ቆፍጣናው ጎንደሬ ዳሽን ቢራን ወይ ንክች! ወይ ፍንክች ያባ ቢለዋ ልጅ! ይልቁን ጠላ ቤቱ ገብቶ እንዲህ እያለ ያስዘፍን ገባ።

ሁመራ ሳይመጣ፣
ወልቃይት ሳይመጣ፣
ወያኔ ሳይወጣ፣
ጠገዴ ሳይመጣ፣
ውሻ ብለህ ጥራኝ ዳሽንን ብጠጣ

ብሎት እርፍ! ይኸን ያህል ካዝናናሁአቸው በኋላ ወደ ተነሳንበት ርዕስ ለመልሳቸው። ዕውነቱን ለመናገር ከርእሱም አልወጣሁም። ሁለቱን ታሪክ ያመጣሁት እንጂነየራችን ከዚያ ሰነፍና ከአይርቤ ባል እንጂ ከቆፍጣናው ጎንደሬው አለመሳሰል ስላሉኝ፤ነው።



ምናልባት ኢንጅኒይር ኃይሉ፣ “የምርጫ ሥነ-ምግባር ድንቡን አስለውጨው! አስለውጨው”እያሉ እንደዚያ ሰነፍ ባል ይመጻደቁብን ይሆናል። አይይ!!! ምነው በተውን። እንኳን ይኸን “የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ” ማታለያ ሰነድና እራሱ ለፈጠረው ሕገ መንግሥስትም ወያኔ ተገስቶለት አያውቅም። የረቀቀ ጥሩ ሕግማ መች ጠፋ። ያውም ሚሊዮን ዶላር እየተከፈላቸው ፍረንጆች ናቸው የሚያረቁት። ወያኔ ዜጎቹ “ሲያጠፉ” እንዲቀጡበት እንጂ፣ እሱ ሊገዛበት አይደለም ሕጉን ሁሉ የሚያወጣው። በዚያ ሕግ ቢተዳደርማ ኑሮ በምርጫ 97 ሲሸነፍ አንገቱን ደፍቶ ሕይወት ሳያጠፋ ለተመራጩቹ ወንበሩን በለቀቀ ነበር። ሕጉ ለሌሎች መቀጣጨ ዱላ እንጂ ወያኔ ከቁብ አይቆጥረውም። ሕጎቹ በሙሉ የዓለም አቀፍ ደረጃ ጠብቀው የተነደፉት፣ የዓለምን ሕብረተሰብ ማጭበርበሪያ እንጂ፣ ሌላ ፋይዳ የለውም። አይመለከታቸውማ! ይኸም የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ፣ እነ እንጂንየር ኃይሉ ይተዳደሩብት እንደሆነ እንጂ፣ መለስ የሚገዛው በደደቢት ሕግ ብቻ ነው። ያውም ሕገ አራዊት ነው።

እነ ኢንጅኒየር ኃይሉ፣ የምርጫው ሥን-ምግባር ደንብ፣ ከወያኔ የተረፈ ፍርፋሪ ይወረወርላቸዋል። ግራም ነፈሰ ቀኝ እንጂንየሩ ወኔአቸው ፈሶ በገዛ ፈቃዳቸው የተማረኩ አስመሰላችሁው እንጂ ለውጥ እንደማያመጡ እሳቸውም መረዳት የሚያቅታቸው አይመስለም። እርግጥ ወያኔ ጉያ ውስጥ መግባት አንድ ጥቅም አለው። አቶ ልደቱ አያሌው ወያኔ ጉያ ውስጥ ባይገባ ኑሮ፣ ሕዝቡ እንድ ቅርጫ ተቀረማምቶት ይዘለዘለው ነበር። ወያኔ

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የመከላከያ ሽፋን ስለሰጠው መኖር ቻለ። ኑሮ ተባለና! የተወረወረለትን እየተቀበለ ዛሬ ድርሶ ድል ተቀዳጅቷል። ልደቱ ያኔ የወሰደው እርምጃ ትክክል መሆኑን ዛሬ እንጂነየር ኃይሉ አረጋግጠውለታል። ያ የሚያመለክተው፣ ምናልባት ኃይሉና ልደቱ በኢ.ድሜ ይለያዩ እንጂ፣ ውሳኔ ሲውስኑ አንዱ ቀደሞ ሌላው ዘግየ እንጂ በተግባር አንድ አንድ ነበሩ ማለት ነው። የሚጠቀማቸው ከመሰለ፣ ለወንድሞቻቸው ቅንጣት ታህል ደንታ የላቸውም። አሁን የምንጠብቀው፣ አደባባይ ወጥተው፣ "ለደቱ ልጄ! በድዬህለሁ ይቀር በለኝ" ማላታቸውን ብቻ ነው።

ዛሬ የወያኔ ካምፕ ጨቤ እየረገጠ ነው። "ምነው" ቢባል "እንደዛሬ በለስ ቀንቶት አያውቅም" ነው መልሱ! በየጊዜው ከተቃዋሚው ጎራ እየበረገጉ ብዙ ሰዎች ተጠምደው ወጥመዱ ውስጥ ሰተት ብለው ገብተውለታል። ለምሳሌ አንዱ "ወይ ያኔ! ወይ ያኔ! አንተን አያርገኝ የዚያን ቀን መጥኔ" ብሎ እንዳልዘፈነባቸውና ጀግናችን ብለን እንዳላወደስነው፣ በጥቅም ተታሎ ወያኔ ጉያ ገብቶ አሳፍሮናል። ያኔ አሾፈብን እንጂ እነሱ ባገኙት ድል ብዙም አልጨፈሩም። ከተቃዋሚው ወገን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዳጣሉት ከተረዱ በኋላ ጥፊ አልሰውት በ "ካልቾ" ረገጠውት እንደሞተ ሰው ጥለውታል። ኢንጂኒየር ኃይሉ ግን ልዩ ግኝት ናቸው። ጨጉላው አብቧል ዛሬ፣ ጨጉላው አብቧል ዛሬ ኢእይተደለቀ ነው! እኛ አፍረናል፣ ወያኔ ይጨፍራል። በየ አይጋው፣ በየዋልታው "ጉሮ ወሻባዬ" እየደለቁብን ነው። የአሁኑ ይባስ! ወያኔ እንዲህ ዓይነት በለስ ቀንቶት አያውቅም። ትልቁን አሳ ነበሪ የወያኔ ኣትማጆች ጎትተው ያወጡት እያሉ ባለ ካርቱኖች ስሜታቸውን በስዕል እያቀረቡት ነው።




ሱልጣን ራያ ከመጣው ኢ.ኢ.ድን
የመልዕክት መለዋወጫ የተወሰደ

ኅብረት፣ አንድነት፣ መስማማት በእርግጥ አስፈላጊ ነው። መመካከር፣ መነጋገር በዕርግጥ ጥሩ ነው። ቁም ነገሩ የፈረሙት ሰነድ አይደለም። ተመካክረው ምን ያረጉት ነገር ምን አይሆንም ነው የሚባለው? "አንድነት ከማን ጋር?" የሚለው ጥያቄ ወቅታዊ ነው። መኢአድ ከኢህአፓ ጋር አንድነት ቢፈጥር ያምርበታል። ኢህአፓም መኢአድም ኢትዮጵያን ሊያጠፋት ከተነሳው ጠላት ጋር ተፋላሚ ነበሩዋ! መኢአድ ከአንድነት ጋር ሕብረት ቢፈጥር ያምርበታል። ሁለቱም በአካሄድ ቢለያዩ እንጂ ለአንድ ዓላማ የቆሙ ነበሩዋ! አንድነት ከግንቦት ሰባት ጋር፣ ወይም ከመኢሶን ጋር ቢተባበር አይደንቅኝም። መኢሶም፣ ግንቦት ሰባትም ወያኔን ይቃወሙታላ! መኢአድ

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

አልፎ ተርፎ ትላንት ሲገድሉን ከነበሩት የደርግ ሰዎች ጋርም ቢገጥም ባልገረመኝ ነበር፣ ምክንያቱንም እንዚያ አምባገነኖች ሥልጣናቸውን ለመጠበቅ ብዙ ሰው ገድለዋል እንጂ አገር እንደወያኔ ሸንሽነው አልሸጡም። ሱዳን ድንበር ያለው ድንበራችን ሂዷል እኮ! መሀል አገር ያለው የርሻ ቦታ ተሸጦ አልቋል እኮ! የደርግ ሰዎች ትላንት ያጠፉት ጥፋት እንደተጠበቀ ሁኖ፣ ዛሬ ግን ኢትዮጵያን ለመታደግ በየጊዜው መስዋዕት የሚከፍሉ ከመሀከላቸው አልጥፉማ! ከወያኔ ጋር ግንባር መፍጠር ግን፣ የክህደት ከህደት ነው። ይቅርታም የማይደረግለት ጥፋት ነው። ዝም አንበል!

ለማጠቃለል ያህል፣ እንጂንየሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥይቄ ወደ ጎን ትተው፣ አገር ወዳዱን ወገናቸውን ክደው፣ ሕዝብን ከሚያደማ፣ አገርን ከሚያጥፋ፣ አምባ ገነን ፋሽስት መንግሥት ጋር ተሻርከዋል። እሳቸውም ያንን አያጡትም፣ ደጋፊዎቻቸውም ያውቁታል። ሕዝቡም ያውቀዋል። አሁን ማንን ለማታለል ነው የሚሞክሩት? ለመሆኑ፣ አሽቃባጬቻቸው "መኢአድ ብዙ ጥያቀ ለኢሃዴግ አቅርቦ ተሳክቶለታል" ሲሉን፣ ማን ሞኝ አለ የሚቀበላቸው? የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆነ እንኳን እንዲህ በግልጹ ሲሸጡት፣ ሲዋዋሉብትም ያውቃል። ስታመካኝ ብላኝ ነው ያለች ያች እንስሳ? ጨረስኩ።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com